# አገር መውደድ ማለት

***

*ክንፈ ሚካኤል (ለየካቲት ፳፮ ዓ/ም)*

አገር መውደድ ማለት ምንድነው ትርጓሜው[1]
ማሰር መግደል ነወይ ጦርነት ፍጻሜው።

አገር መውደድ ማለት ምንድነው ትርጉሙ
መስከር መንደድ ነወይ ሰርክ እየቆዘሙ።

አገር መውደድ ማለት ምንድነው ነገሩ
ማጥፋት ማውደም ነወይ የቆመን ከስሩ
ወገን ማራቆት ነው ለራስ እየሰሩ።

አገር መውደድ ማለት ምንድነው ሀሜታው
መለዛለዝ ነወይ ጥድፊያና ቱማታው።
አገር መውደድ ማለት ምንድነው ብላቱ
መሰዳደብ ነወይ ጦር መስበቅ በብርቱ።
ልብ መስበር ነወይ አንገት ማቀርቀሩ
መወራረፍ ነወይ ቀርቶ መፋቀሩ።

አገር መውደድ ማለት ዋነኛ ትርጓሜው
ሁሉንም ባንድ ይዞ መጓዝ ነው ስያሜው።
አገር መውደድ ማለት ትርጉሙ ምንድነው
አፊጫን ሲመቱት ዐይን ማልቀሱ ነው።
አገር መውደድ ማለት አብይ ቁም ነገሩ
ከራስ በላይ ወገን ይቅደም ነው ምስጢሩ።

አገር መውደድ ማለት ሶስተኛ ትርጉሙ
በነፍስ ወከፍ ቀርቶ ባንድ ላይ መዝመሙ
በሚቻለው ሁሉ ወገንን መጥቀሙ።

አገር መውደድ ማለት ቀናኢ ትርጉሙ
ካለፊው ስህተት ትምህርት እየቀሰሙ
መሠረት መጣል ነው ላጭር ለረጅሙ።

አገር መውደድ ማለት ውስጣዊ ስሜቱ
ለወገን መሞት ነው ተዋግቶ በብርቱ።
አገር መውደድ ማለት ቀላል ነው ሚስጥሩ
ጠላትና ወገን መለየት በጥሩ
ኋላ በጥርቆ ለመጣል እያነጣጠሩ።
እንደ ሰሜንና እንደ ምስራቅ ጦር
አጥንት መከስከስ ነው በጫካ በዱር።

ሌላው በሚመቸው ተቢጤው ተባብሮ
አይዞን መባባል ነው ከወገኑ አብሮ።
ለነገ ዛሬ ነው ማለም መተለሙ
ችላ ማለት የለም ያን እስኪፈጽሙ።

ስለዚህ ወዳጄ !!!
አገር መውደድ ማለት መባከን አብሮ እንጂ
እንደ ዐይን እንደ ጆሮ እንደ እግር እንደ እጅ።

አገር መውደድ ማለት ባያሌው ብዙ ነው
አማሪት[2] ደምጻዊው የሚያንጎራጉረው
ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚያከናውነው።

የካቲት ፳ቀን ፪ሺህ ፪ዓ/ም
ሚልበርን፣ አውስትራሊያ

---

[1] ጌታ መሳይ አበበን ያስታውሷል
[2] አማሪት ማለት ሴት ዘፋኝ፣ አቀንቃኝ ድምጻዊት ማለት ነው አለቃ ኪ/ወ/ክፍሌ